የወ/መ/ቁጥር 160013

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አቶ አሚር ከማል መሐመድ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ነሐሴ 06 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የሌላውን ሰው አካል ለመጉዳት አስቦ ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ልዩ ቦታው ሻሸ ካባ አካባቢ የግል ተበዳይ አቶ አብርሀም ጀዳን በቧንቧ ብረት አንድ ጊዜ የቀኝ እጁን እና አንድ ጊዜ የኋላ ጭንቅላቱን በመምታት ህመም እንዲሰማው እና ጭንቅላቱ እንዲያብጥ በማድረጉ በፈፀመው ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችን ቃል ፍ/ቤቱ እንደመረመረው በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ ተከሳሽ የግል ተበዳይን በዱላ ነገር በመምታት ጉዳት ማድረሱን አንደኛ ምስክር(የግል ተበዳይ) ሲያረጋግጥ፤ ሁለተኛው ምስክር ደግሞ በወቅቱ ተከሳሽ የግል ተበዳን ይዞት ነበር፤ ነገር ግን በምን እንደመታው አላየሁም በማለት ያስረዳ ሲሆን ከዚህ ለመገንዘብ የሚቻለው ተከሳሽ በክሱ ላይ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን ስለሆነ ተከሳሽ በተከሰሰበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር እንዲከላከል ተነግሮት፤ ነገር ግን ተከሳሽ በተደጋጋሚ ጊዜ የመከላከያ ማስረጃ ለማቅረብ ባለመቻሉና መጥሪያ አንኳ ወጪ ያላደረገ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የተከሳሽን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት አልፎበታል። ይህ ማለት ደግሞ ተከሳሽ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ለማስተባበል የማይችል መሆኑን ስለሆነ ተከሳሽን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፣ የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ምክንያት የለም፤ ነገር ግን ግራቀኙ

ታርቀው የቀረቡ መሆኑ ከግምት ውስጥ ፍ/ቤቱ እንዲያስገባው በማለት

አመለከተ።

ተከሳሽ፣ ዕድሜዬ 19 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 9 ኛ ክፍል ነው፤ ትዳርና

ልጅ የለኝም፤ ገቢዬ መኪና በማጠብ በቀን ከብር 20-30 ድረስ

አገኛለሁ፤ ከግል ተበዳይ ጋር ታርቀን በሰላም እየኖርን ነው ሲል፤ የግል

ተበዳይም ቀርበው መታረቃቸውን አረጋግጠዋል።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

ውሳኔ

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ጥፋተኛ የተባሉበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 5 ነው። ስለሆነም የዚህ እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጥን/range/ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ የወሰነው መነሻ ቅጣት ሰባት ወር ከአስራ አምስት ቀን ቀላል እስራት ነው።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 ወይም 85 መሰረት የቅጣት ማክበጃ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የመነሻውን ቅጣት እርከኑን ከፍ ሳያደርግ እንዳለ እርከን 5 ን ወስዶታል።

ተከሳሻ በበኩላቸው የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 ላይ በተመለከቱት መሰረት በማስረጃ የተደገፉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አላቀረቡም፤ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የቅጣቱን እርከን ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆም በማክበጃ ምክንያቱ መሰረት ከፍ ያለ እና በማቅለያ ምክንያትም ዝቅ ያለ ስለሆነ ከላይ በተወሰነው መሰረት ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በሰባት ወር ከአስራ አምስት ቀን ቀላል እስራት እንድትቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽና የግል ተበዳይ በአሁኑ ወቅት ታርቀውና በሰላም እየኖሩ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት የእስራት ቅጣቱ ከሚፈፀም ይልቅ ለተከሳሽ አንድ ዕኩ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ፀባይና አመሉ ወደፊት ቢታይ መልካም ስለሆነ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሦስት ዓመት ገደብ አግዶታል።

2 ኛ. ተከሳሽ ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ ለብር 600.00(ስድስት መቶ ብር) የሚበቃ ዋስትና ትጥራ። በዚህም መሰረት ቀደም ሲል ለዋስትና ያስያዘው ገንዘብ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) መሰረት እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ባለበት እንዲቆይ ታዟል።

3 ኛ. ተከሳሽ ለፅህፈት ወጪ ብር 30.00(ሰላሳ ብር) ለመንግስት ይከፈል።

4 ኛ. ተከሳሽ የፅህፈት ወጪ የተባለውንና የመተማመኛ ዋስትናውን ሲከፍል ይለቀቅ።

5 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

6 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።